በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ነሐሴ 15, 2011
አዲስ አበባ
ጋዜጣዊ መግለጫ

## 'ጳጉሜን በመደመር' ሀገራዊ መርሐ ግብር ቅድመ ዝግጅት በመካሄድ ላይ ነው፡፡

ኢትዮጵያን በሚቀጥሉት ዓመታት በመደመር እሳቤ አንድነቷንና ብልጽግናዋን እውን ለማድረግ አዲስ ምእራፍ ጀምራለች፡፡ የመደመር ስድስት ምሰሶዎችን የሰነቀ የጷጉሜን በመደመር ሀገር አቀፍ መርሐ ግብር ዝግጅት በመካሄድ ላይ እንደሚገኝ በጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ተገለጸ፡፡

የተለያዩ የመንግስት አካላት የየዕለት እንቅስቃሴዎቹን ለማቀድ፣ ለመምራት፣ ለማስተባበርና ለማስፈጸም ኃላፊነት የወሰዱ ሲሆን ዝግጅትና አካሄዱንም በተመለከተ ለህዝብ በተለያዩ መንገዶች የሚያሳውቁ ይሆናል፡፡

በዚሁም መሰረት የቀናቱ ስያሜና የአስተባባሪዎቹ ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ጷጉሜ 1፡ ብልጽግና (የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት)

ጷጉሜ 2፡ ሰላም (የሰላም ሚንስትር ክብርት ሙፈሪያት ካሚል)

ጷጉሜ 3፡ ሀገራዊ ኩራት (የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ኢ/ር ታከለ ኡማ)

ጷጉሜ 4፡ ዴሞክራሲ (የትራንስፖርት ሚንስትር ክብርት ዳግማዊት ሞገስ)

ጷጉሜ 5፡ ፍትሕ (የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ክቡር ብርሃኑ ፀጋዬ)

ጷጉሜ 6፡ ብሄራዊ አንድነት (የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት)

በዚሁ አጋጣሚ ህብረተሰቡ በተለያዩ ዝግጅቶች በመሳተፍ ሀገራዊ ብልጽግናን፣ ሰላምን፣ ሀገራዊ ኩራትን፣ ዴሞክራሲን፣ ፍትሕንና ብሄራዊ አንድነትን በማሳደግና በማበልጸግ ወደ መጪው አዲስ አመት ተስፋ ሰንቆ ለመሸጋገር ይሁነኝ ብሎ እንዲሰራ ጥሪ ቀርቧል፡፡

//